# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል
## 14 ኛ ሳምንት
## ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ለማውጣት መራቸው

**ዓላማ**

- ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ለማውጣት እንዴት እንደመራቸው መማር፡፡

**ምንባባት**

- ዘጸ 3፣5፣13 እና 14 ፣

**መግቢያ**

- በዛሬው ትምህርታችን ሙሴ በፈርኦን ቤት የነበረውን የክብር ኑሮ በመተው እስራኤልን ነፃ ለማውጣት በእግዚአብሔር መመረጡን እንማራለን፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. ሙሴ የት አደገ? 2. በፈርኦን ቤት መኖሩን እንዴት አቆመ?

**ትምህርት፣**

- ሙሴ የፈርኦን የልጅ ልጅ ተብሎ በቤተመንግሥት አደገ፡፡ እያደገም በእስራኤል በሚፈጸመው በደል ያዝን ነበር፡፡ ያዘነው ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ግብፃውያን ባሮች አድርገዋቸው ስለነበር ነው፡፡ ከዚያም አንድ ግብፃዊ ሌላ እስራኤላዊን ሲገድል አይቶ ሊያድነው የሠራው ሥራ ስለታወቀበት ሙሴ ከፈርኦን ቤት እና ከግብፅ ሸሽቶ ወደ ምድያም ምድር ሄደ፡፡
- ሚስት አግብቶ በአማቹ ቤት ከብት እየጠበቀ በእረኝነት ኖረ፡፡
- አንድ ቀን ሙሴ ***«ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ»፡፡*** በዚህ የተደነቀው ሙሴ ይሄን ለመመርመር ወደ ተራራው ሄደ፡፡
- ወደእሳቱ ሲቀርብም ***«ሙሴ ሙሴ የቆምክበባት ምድር የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ፡፡…….. እኔ እግዚአብሔር ነኝ የአባቶችህ አምላክ፣የአብርሐም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብም አምላክ ነኝ»*** የሚል ድምፅ በቁጥቋጦው መሐል ከሚነደው እሳት ሠማ፡፡
- ወደ ቤተክርስቲያን ስትግቡ ጫማችሁን ታወልቃላችሁ? ለምን እንደሆነ አስረዱ
- እግዚአብሔር የሕዝቡን ለቅሶ እንደሰማ ለሙሴ ነገረው፣ እስራኤልንም ነፃ ለማውጣት ላከው፡፡ከእርሱ ጋር እንደሚሆንም ነገረው፡፡ሙሴም ወደ ፈርኦን ሄዶ ***«የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ሕዝቤን ልቀቅ ይልሃል፡፡»*** አለው፡፡
- ፈርኦን ግን እንዲሄዱ አልፈለገም እግዚአብሔርም ብዙ ቅጣቶችን በፈርኦንና በግብፃውያን ላይ አወረደ፡፡ ታላቅ ተዓምራትም አሳያቸው፡፡ የፈርኦንን ልጅ ጨምሮ የግብፃውያን የመጀመሪያ ልጆች/በኵር ልጅ/ በመሞቱ ፈርኦን በመጨረሻ ሕዝቡ እንዲወጡ ፈቀደ ፡፡
- እስራኤልም በግብፅ የነበራቸው ንብረት ሁሉ ሰብስበው እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ወደማለላቸው ምድር ለመውጣት ጉዞ ጀመሩ፡፡
- ቀይ ባህር ሲደርሱ ግን ፈርኦን ሓሳቡን ቀየረ እስራኤልን እንዲመልሱ ሠራዊቱን በሙሉ ላከ፡፡ ሕዝበ እስራኤል ከኋላ ሠራዊቱን ከፊት ቀይ ባህርን ሲያዩ መሄጃ ስላልነበራቸው በሙሴ ላይ ጮኹ፡፡
- ሙሴም ሕዝቡን ***«የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ»*** አላቸው፡፡ ባህሩንም በበትር መታው፡፡ ምን እንደሆነ ገምቱ ባሕሩ ወዲያውኑ ለሁለት ተከፈለ፡፡ የሚያልፉበት ደረቅ መሬትም ተገለጠ፡፡ እስራኤል በደረቅ መሬት ተሻግረው ሲያበቁ፡፡
- የፈርኦን ሠራዊትም ተከትሏቸው ገብቶ ከመሐል ደረሰ፡፡ ሙሴ ዳግመኛ ባሕሩን ሲመታውም ውሃው በደረቀው መሬት ፈሰሰ፡፡ የፈርኦን ሠራዊት ከፈረሶቻቸውና ሠረገሎቹ ጋር በቀይ ባሕር ሰጠሙ፡፡
- እስራኤልም እግዚአብሔርን በመዝሙር አመሰገኑ፡፡ ***«በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ፤»***

| **መዝሙር** | **ትርጉም** |
|---|---|
| ንሴብሖ (2) ለእግዚአብሔር | እናመስግነው (2) እግዚአብሔርን |
| ስቡሓ ዘተሰብሐ | ምሥጉን ነው የተመሠገነ |

**ይቆየን፡፡**